ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991


# መለዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር ሁለት ታሕሣሥ 2012 ዓ/ም


## ከፍ ያለ ስም

አቶ ዓምኃ መኮንን

## ሰዋዊ

ኀዳጣን

## ቀለም

ኢሰመጉ በመሥራቾች ዕይታ

# የሠሩልንን እናመስግን



# ርእሰ አንቀጽ

ኢሰመጉ

## በነጻ አእምሮ የሚያመዛዝን ወጣት ለአገር ሀብት ነው!

የሰብዓዊ መብቶች ቀን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የተ.መ.ድ) ጠቅላላ ጉባኤ በ1948 ዓ.ም ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ባጸደቀበት ዲሴምበር 10 ቀን በየዓመቱ ይከበራል፡፡ የ2019 ዓ.ም ዓመታዊው የሰብዓዊ መብቶች ቀን Youth Standing Up for Human Rights - «ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የወጣቶች ጥብቅና» - በሚል መሪ ቃል ተከብሯል፡፡ የተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት ይህን መሪ ቃል የመረጠበት ምክንያት በማኅበረሰብ የጋራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የወጣቶችን የመሪነት ሚና ለማጉላትና በወጣቶች ተሳትፎ መጪው ጊዜ የተሻለ እንደሚሆን ተስፋ ለመሰነቅ ነው፡፡

ወጣቶች የመልካም ለውጥ ሐዋርያት የመሆን ዐቅማቸውን ለማክበር፣ ድምፃቸውን ለማጉላት፣ ለመብቶች መከበርና መጠበቅ በሚደረገው ትግል ዓለም አቀፍ ድጋፍ የማሰባሰብ ዓላማ በማንገብ ነው «ለሰብዓዊ መብቶች ጥብቅና መቆም» በሚል ለሰዎች ሁሉ ዓለም አቀፍ ጥሪ የቀረበው፡፡ በተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት በተመራው ዘመቻ መንፈስ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችም ራስን ለሕግ እና ለሞራል ልዕልና ከማስገዛት ባሻገር ለመብቶች መከበር ጥብቅና መቆም፣ ዘረኛነትን፣ የጥላቻ ንግግርን፣ ተጋፊነትን፣ መድልዎንና የከባቢ አየር ለውጥን መቃወምና መከላከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመንግሥት አካላት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም ኅብረተሰቡ ይህ እውን እንዲሆን በሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ የማነቃቃትና ዓላማውን አንግበው እንዴት እንደሚቆሙ በምሳሌ የማሳየት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

ወጣቶች በአገራቸው፣ በአካባቢያቸው እንዲሁም በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ተሳትፎ ማድረግ መቻላቸው ከመሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች መርሖዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሁሌም ቢሆን የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጥ ዋነኛ ተዋንያን እንደመሆናቸው በሕይወታቸውና በደኅንነታቸው ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ በሚያሳድሩ ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው፡፡ በሕዝብ ደረጃ በሚካሄዱ የመልካም ለውጥ እንቅስቃሴዎች ግንባር ቀደም ተሰላፊዎችና ዓለምን የተሻለ ሥፍራ ለማድረግ የሚረዱ አዲስ ሐሳቦችና መፍትሔዎችን የሚያፈልቁ ቢሆኑም ብዙውን ጊዜ በዕድሜአቸው ምክንያት ወደ ጎን ይገፋሉ፤ በመብቶቻቸው እንዳይጠቀሙ የሚያደርጉ ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች ያጋጥሟቸዋል፡፡ አምራች ኃይል የሆኑትን ወጣቶች መብቶች ማክበር፣ እነርሱን በዕውቀት ማነጽና ጠያቂ ዜጎች እንዲሆኑ ማብቃት ጥቅሙ ለአገር ብቻ ሳይሆን ለዓለም የሚተርፍ ነው፡፡

አሁን ባለው የሐገራችን ነባራዊ ሁኔታ ወጣቶች በየክልሉ የሚደራጁበት መንገድ እጅግ በሚያሳስብ ሁኔታ ብሔርን ብቻ መሠረት ያደረገ ሆኗል፡፡ ሕጋዊ ሰውነት ሳይኖራቸው በየሥፍራው የሚንቀሳቀሱ የወጣቶች ስብስቦች በሐገር አቀፍ ደረጃ እያየነው ያለውን የፖሊቲካ ለውጥ ሂደት በማምጣት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከታቸው የማይታበል ሐቅ ቢሆንም እነዚህ ብሔርን መሠረት ያደረጉ የወጣቶች ስብስቦች ለአደገኛ ፖሊቲካዊ ዓላማ ማስፈጸሚያ ሲሆኑ እየታዘብን ነው፡፡

ወጣቶችን ለእኩይ ፖለቲካዊ ዓላማ ማስፈጸሚያነት መጠቀም በኅበረተሰባችን ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ዛሬ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ለነገም ይተርፋል፡፡ የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑት ወጣቶች በተለይም የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አንዳንድ የፖሊቲካ ወትዋቾች የሚያቀርቡትን ስሜት ቀስቃሽ ዲስኩር ሳያመዛዝኑ ዐምኖ በመቀበል አንዳች እኩይ ድርጊት ለመፈጸም ከመነሣታቸው በፊት በአመክንዮ ሁኔታዎችን መመዘን ይገባቸዋል፡፡

ስለሆነም፣ ወጣትነት ሐገር የምትታነጽበት ጡብ ብቻ ሳይሆን የመሠረት ደንጊያም በመሆኑ በነጻ አእምሮ ሁኔታዎችን በማመዛዘን ለመልካም ማኅበረሰብ ግንባታ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ መወጣት አለባቸው፡፡

## መልእክተ ኢሰመጉ

አሳታሚ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች

ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም



### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org


ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሚጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው::

# እ ፍ ታ

## ዜና






### የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጥምረት ተመሰረተ

ገላውዲዮስ ግሩም

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ላይ የሚሰሩ ግለሰቦችን አቅፎ የሚሰራ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጥምረት ተመሰረተ።

ጥምረቱ የግለሰብ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን መብት ለማስከበር እንዲሁም ደንነታቸውን ለማስጠበቅ አልሞ የተመሰረተ ሲሆን በምስረታውም ወቅት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ድርጅቶቾ ህብረት ሊቀመንበር አቶ መሱድ ገበየሁ ሀገራችን ላይ ይህ ጥምረት በመመስረቱ ትልቅ የምስራች ነው ብለዋል።

ጥምረቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው ተሟጋቾች የሰብአዊ መብት ሲጣስ በሚያደርጉት ተቃውሞ ሊደርሱባቸው የሚችሉ የተለያዩ ጫናዎችን ለመቀነስ እንደሚሰራ ተጠቅሷል።

አቶ መሱድ እንዳሉት በቅርቡ የተሻሻለው የሲቪል ማህበራት አዋጅ የጀመረውን መልካም እድል በመጠቀም ከምንጊዜውም በላይ ተሟጋቾችም ሆኑ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በከፍተኛ መነቃቃት መስራት አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

ጥምረቱ በሰባት ግለሰቦች እና በሰባት የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የሚመራ ሲሆን ሃገራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት አሰራር ዘዴዎችን በሚገባ ለመጠቀም የሚያስችል ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶችን እንደሚተገብር ተገልጿል።

በምስረታው የተገኙ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የአባልነት ፊርማ ስነ ሥርአት አከናውነዋል። በቀጣይም የአባላቱን ቁጥር በመጨመር በክልሎች ተደራሽ ለማድረግ

### ኢሰመጉ በእምነት ተቋማት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን አወገዘ

ገላውዲዮስ ግሩም

በሞጣ ተከስቶ የነበረውን የቤተ እምነት ቃጠሎ ተከትሎ ኢሰመጉ ታኅሣሥ 14/2012 ዓ/ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ የቤተ እምነቶችን መቃጠል አወገዘ።

ኢሰመጉ ባወጣው መግለጫ ማንኛውም ሰው የመረጠውን እምነት የመከተል እና የማስፋፋት መብት እንዳለው አውስቶ የትኛውም አካል ሆነ ግለሰብ ማንኛውንም የቤተ እምነት የማቃጠል መብት የለውም ብሏል።

በመግለጫውም ሞጣ ላይ 4 መስጊዶች እና ንብረታቸው የሙስሊሞች የሆኑ ሱቆች እና ንብረቶች መቃጠላቸውን ጠቅሶ መንግስት የደረሰውን ጥፋት አጣርቶ ጥፋቱን ያደረሰውን አካል ለህግ ማቅረብ አለበት ሲል አሳስቧል።

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት በቤተ እምነቶች ላይ እየተከሰቱ ያሉ ቃጠሎዎች እና ጉዳቶች ኢሰመጉን እንደሚያሳስቡት ገልጾ መንግስት ያለበትን የእምነት ተቋማትን የመጠበቅ ሀላፊነት በአግባቡ መወጣት አለበት ሲል አሳስቧል።

ከቅርብ ጊዜዎች ወዲህ በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ እምነቶች የማምለኪያ ስፍራዎች ጉዳት ሲደርስባቸው እያስተዋልን ነው እነዚህ ሁኔታዎች ሀገርን ወደ አለመረጋጋት ውስጥ እሚከቱ መሆናቸውን ማህበረሰቡ ተረድቶ እንዲህ አይነት ተግባራትን እንዲያዎግዝ ጥሪ አቅርቧል።

# “ሰዋዊ”

## ኅዳጣን

በሱራፍኤል ግርማ

ረቡዕ፤ ጥቅምት 12 ቀን 2012ዓ.ም ምዕራብ አርሲ ዶዶላ። በዘርና በሃይማኖት ማዕከልነት የተሰባሰቡ ወጣቶች <<መጤ>> ባሏቸው ዜጎች ላይ የጅምላ ጥቃት መፈጸም ጀመሩ። በዚህ የተደናገጡት የጥቃት ሰለባዎች ለአካባቢው የመንግሥት አካላት የ<<ድረሱልን>> ጥሪ ቢያቀርቡም በጊዜ ምላሽ አላገኙም።

በብሔርና በሃይማኖት ልዩነት ሳያደርግ በግዛት ወሰኑ የሚኖሩ ዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የማስከበር ኃላፊነት ያለበት ምድራዊው መንግሥት ጥበቃ ሊያደርግላቸው ፈቃደኛ ባለመሆኑ የሰማያዊውን መንግሥት ከለላ ሽተው ከመኖሪያ ቀዬአቸው በመሰደድ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለመጠለል፤ አካባቢውን ጥለው ለመሸሽ ተገድደዋል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ክስተት በኢትዮጵያ በተደጋጋሚ የሚከሰት ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ዜጎች ‹‹መጤ›› እየተባሉ ሲገደሉ፣ ለዘመናት ከኖሩባቸው ቀዬዎች ሲፈናቀሉና ሀብት ንብረታቸው ሲዘረፍ በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ያሉ የመንግሥት አካላት ጉዳዩን በቸልታ ሲመለከቱ፣ ከዚያም አለፍ ሲል የድርጊቶቹ አስተባባሪዎችና ፈጻሚዎች ሆነው መቆየታቸው የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡

የ‹‹መጤ›› እና የ‹‹ተወላጅ›› ፍረጃ ይበልጡን እንዲገንን በማድረግ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዋነኛ መንሥኤ ከሆኑ ምክንያቶች መካከል አንዱ የኢፌዴሪ አባል ክልሎች የተዋቀሩት ብሔርን መሠረት ባደረገ አከላለል መሆኑ ነው፡፡ ግለሰቦችን ሰው በመሆናቸው ሳይሆን በተወሰነ ቡድን አባልነታቸው ፈርጆ እውቅና የሚሰጠው ብሔርን መሠረት ያደረገ የክልል አወቃቀር በአንድ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ዜጎችን የክልሉ ‹‹ባለቤቶች›› እና ‹‹መፃተኞች›› አድርጎ ይከፋፍላል፡፡ በዚህም ምክንያት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩ ነገር ግን የክልሎቹ ‹‹ባለቤቶች›› ተደርገው የሚታሰቡት ብሔሮች ተወላጆች ያልሆኑ ዜጎች ኅዳጣን ከመሆን አልፈው በክልል ሕገ መንግሥቶች ዕውቅና ተነፍጓቸዋል፡፡

በአንድ ብሔር በተሠየሙ ክልሎች የሚኖሩ ኅዳጣን በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጣቸው የመምረጥና የመመረጥ፣ የእኩልነት፣ የመዘዋወር፣ የመደራጀት፣ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብቶቻቸውን ሲገፈፉ ይስተዋላል፡፡

የተመድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጽ/ቤት ‹‹ማይኖሪቲስ›› በሚል አርእስት ባወጣው ጽሑፍ በዓለም ላይ የሚገኙ ሐገራት በጠቅላላ በብሔር፣ በጎሣ፣ በሃይማኖት ወይም በቋንቋ ኅዳጣን የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አካትተው የያዙ መሆናቸውንና እነዚህ ኅዳጣን የየማኅበረሰቦቻቸውን ብዝኃነት የሚያበለጽጉ መሆናቸውን ያስታውሳል፡፡ ምንም እንኳ በሁሉም ክፍለ ዓለማት የተለያዩ ኅዳጣን ቢገኙም ብዙዎቹን የሚያመሳስላቸው ጉዳይ በአገራቸው ጉዳይ የመገለልና መድልዎ ሰለባዎች መሆናቸው ነው፡፡

እ.ኤ.አ ከ2008 – 2014 ዓ.ም በተመድ የሰብዓዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር የነበሩት ደቡብ አፍሪቃዊቷ የሕግ ምሁር ናቫኒተም ፒሌይ በ2009ዓ.ም የተከበረውን የሰብዓዊ መብቶች ቀን አስመልክተው እንደተናገሩት በሁሉም ክፍለ ዓለማት የሚገኙ ኅዳጣን ለሥጋት፣ ለመድልዎና ለዘረኛነት ተጋላጮች ናቸው፡፡ እንዲሁም፣ በሚኖሩባቸው አገራት ብዙኃኑ በሚሳተፉባቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና የባሕል ማበልጸጊያ እቅስቃሴዎች ሙሉ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ይገለላሉ፡፡

የሰብዓዊ መብቶችና ለኅዳጣን የሚደረገው የሕግ ጥበቃ ዋነኛ ዓምዶች ከአድልዎ ነጻ የመሆንና የእኩልነት መርሖዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መርሖዎች ከሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች አኳያ ለሰዎች ሁሉ ተግባራዊ የሚደረጉ ሲሆኑ በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በብሔር ላይ ተመሥርተው የሚፈጸሙ መድልዎችን ይከለክላሉ፡፡ እነዚህን ሁለት መርሖዎች በማክበር የኅዳጣንን በውሳኔ የመስጠት ሂደት ውስጥ የመሳተፍ መብት ጨምሮ ለበርካታ የሰብዓዊ መብቶች መከበር አመቺ ሁኔታን መፍጠር ይቻላል፡፡ የኅዳጣን መብቶች መከበር በአንድ አገር ውስጥ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ ለዘላቂ ሰብዓዊ ብልጽግና፣ ለሰላምና ደኅንነት መረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ የእነርሱን ውጤታማ ተሳትፎ ማረጋገጥና የሚፈጸምባቸውን መገለል እንዲያበቃ ማድረግም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎችን በማክበር ብዝኃነትን እንደ ጸጋ መቀበል ይጠይቃል፡፡

የሲቪልና የፖሊቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 27 ለኅዳጣን መብቶች ጥበቃ ያደርጋል፡፡ በጎሣ፣ በሃይማኖት ወይም በቋንቋ ላይ የተመሠረቱ አናሳ ማኅበረሰቦች ባሉበት አገር ውስጥ የእነዚህ አባል የሆነ ሰው ከሌሎች የማኅበረሰቡ አባላት ጋር በባሕሉ እንዳይጠቀም፣ በሃይማኖቱ እንዳያምን ወይም አምልኮውን እንዳይፈጽም፣ ቋንቋውን እንዳይጠቀምበት መብቱ ሊገፈፍ እንደማይችል በቃል ኪዳኑ ላይ ሠፍሯል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን አገራት ተገቢውን የሕግና ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ የኅዳጣንን መብት እንዲያስከብሩ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው የተመድ የኅዳጣን መብቶች መግለጫ ነው፡፡ የመግለጫው አንቀጽ አንድ ‹‹መንግሥታት በግዛት ወሰኖቻቸው የሚገኙ ኅዳጣንን የብሔር፣ የባሕል፣ የሃይማኖት እንዲሁም የቋንቋ ማንነት መጠበቅና ይህ ማንነታቸው የሚጎለብትበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለባቸው፡፡›› በማለት ይደነግጋል፡፡ምንም እንኳ ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ብዝኃነትን ለማስተናገድና የሕዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለማስከበር ምቹ መደላድል ስለሚፈጥር ከሌሎች የመንግሥት አወቃቀር ዓይነቶች ይልቅ ተመራጭ ቢሆንም በጥንቃቄ ሊያዙ የሚገባቸው ጉዳዮችን አስከትሎ የሚመጣ ነው፡፡ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ ዕድሎችን ለመቆጣጠር በሚደረግ ፉክክር የተነሣ በክልል ተወላጆችና ‹‹በመጤዎች›› መካከል ግጭቶች ሲከሰቱ ታዝበናል፡፡

2012ዓ.ም የምርጫ ዘመን ነው፡፡ የዘንድሮው ምርጫ እስካሁን እንዳየናቸው ምርጫዎች የአንድ ወገን የበላይነት ወይም ጠቅላይነት የሚንጸባረቅበት እንደማይሆን ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡ የመንግሥት ሥልጣንን ለመያዝ የሚደረገው ፉክክር በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ብቻ ሳይሆን ድርጅቶቹ ‹‹ይወክሏቸዋል›› ተብለው በሚታሰቡ ማኅበረሰቦችም መካከል ጭምር እየሆነ መምጣቱን እየተመለከትን ነው፡፡ በዚያውም ልክ ፓርቲ አከል የሆኑ ግለሰቦች በፖሊቲካው ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ መፍጠር የሚችሉበትን ዕድል አግኝተዋል፡፡ በጣም አሳሳቢው ጉዳይ የፖሊቲካ ድርጅቶቹ ፉክክር ማየል ወይም የተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦች መግነን ሳይሆን ከእነዚህ የፖለቲካ ዘዋሪዎች ብዙዎቹ ትኩረት በሚያደርጉባቸው አካባቢዎች ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚጠቀሙበት መንገድ ከአድልዎ ነጻ የመሆንና የእኩልነት መርሖዎችን በመጣስ ኅዳጣንን ለጥቃት የሚያጋልጥ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም፣ በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አካላት እንዲሁም የፖለቲካ ተዋንያን በዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖችና በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እውቅና የተሰጣቸውን ሰብዓዊ መብቶች በማክበር ‹‹ወገኔ›› ብለው የሚቆጥሩት ብሔር ተወላጅ ያልሆኑ ዜጎችን በተለይም ኅዳጣንን ከጥቃት እንዲከላከሉ ማሳሰብ ግብዝነት አይሆንም፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።



# የሡሩልንን እናመስግን

ገላውዲዮስ ግሩም

1986 ዓ/ም የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ጨርሰው እንደወጡ አሁን ድረስ እራሳቸውን ሰጠው የሚሰሩትን የሰብዓዊ መብት ስራ እስከ መጨረሻው እንዲገቡ ያስገደዳቸው ችግር ተፈጠረ፡፡

ያኔ ጋዜጠኛ ወንድማቸው በጋዜጣ ላይ የሚያወጣው ነገር ብቻ ምክንያት ሆኖ በመንግስት ይታሰራል እርሳቸውም በወቅቱ አራዳ ፍ/ቤት እየተገኙ የጊዜ ቀጠሮ ሢጠየቅበት፣በየጊዜው እጁ በሰንሰለት ታስሮ ከመኪና ለመውጣት እና ለመውረድ ሲቸገር አስተዋሉ ያኔ ታዲያ <<ሰው እንዴት ሓሳቡን በመግለጹ ብቻ ይታሰራል?>> ብለው ራሳቸውን ጠየቁ፡፡ ቤተሰቦቻቸው እንደሚሉት ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ለተበደለ መቆም (መከራከር )የሚቀናቸው እኚህ የያኒው ብላቴና የአሁኑ ጉምቱ የሰባዊ መብት ተከራካሪ አቶ ዓምኃ መኮንን ገና ከልጅነታቸው ከተበደለው ጎን መቆም የለመዱ ወንድማቸው ላይ የደረሰውን ሲያዩ ሰተት ብለው ወደዚህ የሰው ልጆች መብት መከበር ደንታ ወደሚሰጠው የስራ መስክ ለመግባት ምክንያት ሆናቸው።

ትውልድና እድገታቸው በመሀል አዲስ አበባ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ይሁን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን  በተፈሪ መኮነን ት/ቤት ተከታትለው 1981 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመቀላቀል በህግ ትምህርት ክፍል ተመርቀዋል፡፡ በህግ ትምህርት ቤት ቆየታቸው የህግ ፍልስፍና ትምህርት በሚገባ እንደቀርፃቸው ይናገራሉ የህግ ትምህርታቸውን በ1985 ዓ.ም እንዳጠናቀቁ ልዩ ዐቃቢ ህግ በሚባል ቢሮ የስራውን አለም ሀ ብለው ተቀላቀሉ በዚያም 6 ወራትን ብቻ ቆይተው የያኔው ፍትህ ሚኒስቴር የአሁኑ ጠ/አቃቢ ህግ ቢሮ በመግባት ከጀማሪ አቃቢ ህግነት እስከ ም/ረዳት  ጠ/አቃቢ ህግነት አገልግለዋል <<በተለይ...>> ይላሉ እሳቸው ሲናገሩ ፖሊስ ህጉን ጠብቆ የምርመራ ስራውን እንዲሰራ የምርመራ ስልጠና፣የፍትህ ስርአቱን እንዲዘምን እና በአጠቃላይ የአቅም ግምባታ ላይ ብዙ ሰርተዋል ፡፡ብሎም በዚሁ ቢሮ የፍትህ ሚኒስቴር የአ.አ ተጠሪ ጽ/ቤት ሀላፊ ሆነው አገልግለዋል፡፡

ታዲያ ከልጅነታቸው በውስጣቸው ያደገው ለሰዎች መብት መከራከር በእውቀት የሳድጉት ዘንድ በ 2001 G.C ወደ እንግሊዝ ሀገር አቀኑ እንግሊዝ ሀገር ESSEX ዩኒቨርስቲ በ "Human Right Study" ሁለተኛ ድግሪያቸውን ተቀብለው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል፡፡

በሀገራችን በ1997 ዓ/ም ተነስቶ በነበረው ግርግር የፍትህ ስርአቱም ለመንግስት ፍፁም ታማኝ በነበረ በዚህ ወቅት ከህግ የፈነገጡ ስራወችን አይተው ማለፍ ባለመቻላቸው በዚያው አመት ከፍትህ ሚኒሰትር ጋር በግልፅ ተለያዩ።

በዚህ መሃልም ዩኒቲ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና ቅ/ማርያም ኮሌጅ ለ 6 አመታት በማስተማር አገልግለዋል፡፡ ነገር ግን ከ1997 ምርጫ በኋላ እየተባባሰው የመጣው የመንግስት ግልፅ የሆነ ጭቆና እና አፈና ከልጅነታቸው ጀምሮ በውስጣቸው ያደገው ለፍትህ መቆም በህግ ት/ቤት እንዲሁም በውጭ የሰባዊ ትምህርት ጎልብቶ አፈናውን እንደብዙዎቹ የሙያ አጋሮቻችን  አይተው እንዳላዩ እንዲሆኑ አልፈቀደላቸውም። በዚህም በዚያን ወቅት አስፈሪ የነበሩትን የወንጀል ጉዳዮች በመያዝ መንግስት አሸባሪወች በማለት ለከሰሳቸው

# ከፍ ያለ ስም

ሰዎች ጥብቅና በመቆም መንግስት ከሳሽ እርሳቸው ተከራካሪ ሆነው ተሰየው፡፡

በዚያ አስቸጋሪ በሆነው ወቅት ለጋዜጠኞች፤ለጦማሪያን ፤ለፖለቲከኞች በአጠቃላይ መንግስት ያለአግባብ አስሯቸዋል ብለው ላሰቧቸው ሰዎች ሁሉ ሳየታከቱ ጉዳያቸውን ይዘው ፍ/ቤት፤እስር ቤት ላይ ታች አሉ፡፡

በወቅቱ ታዋቂ የነበሩ ጉዳዮች ማለትም የዞን 9 ጦማሪያን ክስ፤የአቶ በቀለ ገረባ ፤ሀበታሙ አያሌው፤ ጌታቸው ሽፈራው እና የዋለድባ ገዳም አባቶች ጉዳይ ጥብቅና ቁመውላቸው ከነበሩ ብዙ ክሶች ጥቂቶቱ ናቸው። ከዚህም ባለፈ በየእስር ቤቶች በእነዚህ የህሊና እስረኞች ላይ እየደረሰ ያለውን እንግልት ለአለም አቀፍ ማህበርሰብ በማሳየት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። በነበራቸው የሥራ መደራረብ እና ያለ እረፍት መስራት ከመንግስት ማስፈራሪያዎች እና ዛቻዎች ጋር ተደምሮ ከ 3 ጊዜ በላይ ከፍተኛ የሆነ የጤና እክል እያጋጠማቸው ሆስፒታል ለመተኛት ተገደው ነበር፡፡

ከ1998 በኋላ በመንግስት እየደረሰ የነበረውን የሙብት ጥሰት ብቻቸውን ሊሟገቱት አስቸጋሪ ስለነበረ ለተወሰኑት ጠበቆች የገነዘብ ድጋፍ እያደረጉ በሰባዊ ሙብት ጥሰት ዙሪያ ክሶችን እንዲዙ ያበረታቱ ነበር፡፡

አብዛኞቹ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተዳከሙበት በዚያን ጊዜ በግላቸው ከፍተኛ ሀላፊነትን በመውሰድ ከውጭ ድጋፍ አድራጊ ድርጅቶችን በማምጣት ለፖሊሶች እና ለጠቅላላው የፍትህ ማህበረሰብ በሰብአዊ ሙብት አያያዝ ዙሪያ ስለጠናዎችን ይሰጡ ነበር። በዚያ ተስፋ በሚያስቆርጥ ወቅት ለመንግስት ማስፈራሪያና ጫና ሳይበገሩ በሰብአዊ ሙብት ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉ ሰዎች መካከል ያሳልፋቸዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሆነው እያገለገሉ የሚገኙ ሲሆን ገና ዩኒቨርስቲ እያሉ የኢሰመጉ አባላት የሚከፍሉትን መሥዋዕትነት እያዩ በጣም ይማረኩ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የኢሰመጉ አባል መሆን ይመኙ ስለነበር እድሉን አግኝተው እንደ ኢሮፒያኑ አቆጣጠር በ2016 የእድሜ ዘመን አባል ሆነው ተመዘገቡ። በዚያው አመት በተደረገ የሥራ አስፈፃሚ ምርጫ የቦረዱ ሰብሳቢ ሆነው ተመረጡ ከ 1 አመት በኋላም የቦረዱ ሊቀ መንበር ሆነው ተመረጠው እስካሁን ደረስ እያገለገሉ ይገኛሉ ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የህግ ባለሙያዎች ለሰባዊ ሙብት የሚል ህብረት አቋቁመው በሊቀመንበርነት ከፍተኛ የሆነ ስራ በመስራት ላይ ይገኛሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የጥብቅና ስራውን ጋብ በማድረግ በሌሎች ስራዎች ላይ አየሰሩ ሲሆኑ ከሌሎች ባለደረቦቹ ጋር በመሆን የኢትዬጵያ ድጅታል መብት ህብረት የሚባለል አቋቁመው በሊቀመንበርነት እያገለገሉ ናቸው፡፡

እንዲህ ለሰሯቸው የሰባዊ ሙብት ስራዎችም ከተለያዩ ዐለም አቀፋዊ ድርጅቶች እውቅና ተበረከቶላቸዋል፡፡

በቅርቡም በፈረንሳይ እና ጀርመን ኤምባሲ አማካኝነት በየአሙቱ በመላው አለም ሰብአዊ ሙብት ላይ ሰርተዋል ብሎ ላመነባቸው 16 ሰዎች ከሚሰጠው ሽልማት አንዱ በመሆን ሽልማቱን አግኝተዋል፡፡

ይህ የ ፍራንኮ ጀርመን ሽልማት በሀገራቸው ላይ ሰብአዊ ሙብት እንዲከበር በጽኑ የታገሉ ግለሰቦችን እውቅና የሚሰጥ ሲሆን ለ አቶ ዓምኃመ በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ወቅቶች እራሳቸውን አደጋ ላይ ጥለው ለፍትህ ዘብ በመቆማቸው እውቅና ሰጥቷቸዋል።

ከዚያም በፊት ለዋለድባ አባቶች ላበረከቱ አስተዋፅኦ በአሜሪካ የሚገኝ ድርጅት ሸልሟቸዋል ፡፡

Human right fellow ship prize እና ሌሎችም እውቅናዎችንም አግንተዋል ፡፡

ቢሆንም ግን እሳቸው የእኔ ሽልማት "ወንዶችና ሴቶች ደማቸውን ያፈሰሱበት ትግል ልክ እንዳሁኑ ፍሬ ሲያፈራ ማየት ነው" ይላሉ፡፡

አቶ ዓምኃ ካላቸው መደበኛ ስራ በላይ አሁንም ስለ ሰብአዊ ሙብት በተለያዩ የውይይት መድረኮች ጥናታዊ ጽሑፎች ያቀርባሉ በሚዲያዎች ላይ በመቅረብ ሀሳባቸውን እያጋሩን ይገኛሉ፡፡

ታዲያ እኚህ ሰው ሀገራችን ላይ ለውጥ እንዲመጣ ሰብአዊ ሙብት እንዲያብብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አብርክተዋል በማለት የዚህ ወር የ መልእክተ ኢሰመጉ ከፍ ያለ ስም አምድ ሊያወሳቸው ወደደ። ሰፊውን ታሪካቸውን ባጭሩ ስናጠቃልል ላደረጉት እና ወደፊትም ስለሚያደርጉት ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ከወዲሁ ምስጋናችንን እያቀረብን ነው።

ሰላም።

ዖህ ጽሑፍ የጸሐፊውን ኣቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ኬ ላ

## ሕግ

# አንዳንድ ነጥቦች በረቂቁ የማረሚያ ቤቶች ዐዋጅ ዙሪያ

ጥበቡ ኃ.

በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን መባቻ እንግሊዛዊው የሕግ ፈላስፋ ጄርሚ ቤንታም ጥፋተኞችን በእሥር ማቆየት ይገባል የሚል አዲስ አረዳድ ከማፍለቁ በፊት ዓለም በሕግ ወይም በልማድ ጽዩፍ የነበሩ ድርጊቶችን ፈጽመው በተገኙ ሰዎች ላይ የምትወስደው ቅጣት የሞት አሊያም ከፍተኛ ሥቃይን በሰውነት ክፍሎች ላይ ማድረስን ነበር፡፡ በእርግጥ ጥፋተኞችን የሞት ቅጣታቸው እስኪፈጸም ድረስ ተራ በሚጠብቁበት ቅጥር ወይም ማቆያ ሥፍራ ውስጥ ገድቦ ወይም ጠፍሮ ማቆየት ከክርስቶስ ልደት 400 ዓመት አስቀድሞ ጀምሮ የተለመደ መሆኑን ከታሪክ እንረዳለን፡፡ ታዲያ ጄ. ቤንታም ከጊዜው በተለየ መልኩ የሞት ቅጣትን አብዝቶ ተቃዋሚ በመሆኑ ሰዎችን በመግደል አሊያም ለከፍተኛ ሥቃይ በመዳረግ ከመቅጣት ይልቅ የመንቀሳቀስ መብታቸውን በመገደብና ወደ ወኅኒ በመጣል ራሱ መቅጣት ይቻላል የሚል ሐሳብ ይዞ መጣ፡፡ ከዛን ጊዜ ወዲህ እንዲህ ዓይነት ማዕከላትን በተመለከተ ያለው አስተሳሰብ በየጊዜው አዳዲስ አስተሳሰቦች እየተጨመሩበት ከቅጣት ማዕከልነት እስከ ጥፋተኞችን ማረሚያ ተቋምነት ድረስ የሚዘልቅ ለውጥ ታይቶባቸው እዚህ ደርሰዋል፡፡

በሐገራችን ኢትዮጵያም ለእንደነዚህ ዓይነት ተቋማት ያለን ግንዛቤ ስኁት ስለመሆኑ ብዙ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለማዕከላቱ ከሚሰጣቸው ሥያሜ ብንነሣ ዓለም በቃኝ፣ ዘብጥያ፣ ወኅኒ ቤት፣ ጨለማ ቤት... የመሳሰሉት ሲሆኑ በዚህ ውስጥ ለእነዚህ ዓይነት ተቋማት ማህበረሰቡ የሚሰጠው ግንዛቤ በአብዛኛው ጨለምተኛ እና ሕይወት አልባ የሆኑ እስኪመስል ድረስ መሰረታዊዉን ሰዎችን በእስር በማቆየት የማስተማርና ሌሎች ለጥፋት ያኮበኮቡ ሰዎችን የመግቻ ዓላማነቱን የተቃረነ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሠረቱ በቀደመው ዘመን ሰዎችን አሥሮ ማቆየት ያስፈለገው ለመቅጣት ሳይሆን ጥፋተኛ የተባለው ግለሰብ ላይ ለመፈጸም የታሰበውን ቅጣት እስኪፈጸም ድረስ በጊዜያዊነት ለማቆየት በማሰብ ነበር፡፡ የኋላ ኋላ የወንጀለኞች መቅጫ ፍትሕ ሥርዓት (Criminal Justice System) መጎልበትን ተከትሎ የእሥር ማዕከላት አጥፊዎችን ከማኅበረሰቡ በመነጠልና የአጥፊውን ነጻነት በመንፈግ መቅጣት (Punishment)፤ በቆይታቸዉም በትምህርት፣ በሥልጠና እና በምክር በመሳሰሉት መንገዶች ለወደፊቱ ከመሰል የጥፋት መንገዶች እንዴት ርቀው መኖር እንደሚችሉ የሚያስችሏቸውን እውቀት እና ክሒሎቶች በማስታጠቅ በዘላቂነት ወደ ማቋቋም (Rehabilitation) ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡ ፡

ከዚህ ገዢ ሐሳብ አንጻር የሐገራችንን የማረሚያ ተቋማት ሚና ምን እንደሚመስል ያየን እንደሆነ በርካታ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በቀላሉ መገመት ያስችለናል፡፡ ከላይ በጥቂቱም ቢሆን ለመነካካት እንደሞከርነው እንደ ሐገር ለእንደነዚህ ዓይነት ተቋማት ያለን አመለካከት በራሱ ሸፋፋ ከመሆን አንጻር፣ በዘመናት የሕዝብ እና አስተዳደር የእርስ በእርስ ግንኙነቶቻችን ሂደት ውስጥ የተለማመድናቸው መገፋፋቶች እና ከሌሎችም ምክንያቶች አንጻር "እሥር ቤቶች" ንጹሐን ዜጎች ላይ በደረሱ ፍጹም ሰዋዊ ያልሆኑ ሥቃዮችና በደሎች የሚታወሱ የግፉዓን የሥቃይ ዓምባ ናቸው፡፡ ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያ በተደረገው የፖለቲካ ለውጥ ሳቢያ ከታዩ መልካም የሚባሉ እርምጃዎች መካከል የማረሚያ ተቋማትን አደረጃጀት ማሻሻል፣ የሕግ ማሻሻያዎች መጀመር እና ከምንም በላይ ግን ዜጎች ለዘመናት ሰው በሰው ላይ ያደርጋቸዋል ተብለው የማይታሰቡ ጭካኔዎችን ሲፈጸሙባቸው የነበሩ እንደ ‹‹ማዕከላዊ›› ያሉ ቦታዎችን ወደ ሙዚየምነት ለመቀየር ታስበው የተዘጉበት ኂደት ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ምንም እንኳ በግሌ ቦታው በነበረበት ይዞታ ለትውልድ መማሪያ እንዲሆን ተደርጎ መተላለፍ ይገባው ነበር የሚል አቋም ቢኖረኝም፤ ኂደቱ ግን መንግሥት ይኼን ዓይነት የግፍ ቦታዎች ላይ ያለውን አቋም የሚያሳይ በመሆኑ በሁሉም የሐገሪቱ አካባቢዎች ባሉ ተመሳሳይ ቦታዎች ላይ እርምጃ ይወስዳል የሚል ተሥፋ እንዲኖረኝም አድርጓል፡፡

ለመነሻ ከላይ ያለውን ካልን አሁን ደግሞ በ1995 ዓ.ም ወጥቶ የነበረውን የፌደራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ዐዋጅ ቁጥር 365/95 ለማሻሻል በዝግጅት ላይ ስላለው ረቂቅ ዐዋጅ አንዳንድ ነጥቦችን እናንሣ፡፡ ከዚህ አንጻር በሥራ ላይ ያለው ዐዋጅ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት እና በሌሎችም የሐገሪቱ ሕጎች እንዲሁም ስለ ሕግ ታራሚዎች ሐገራችን ፈርማ ያጸደቀቻቸው የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ሥር የተቀመጡ ድንጋጌዎቸን እና መሥፈርቶችን ሊያሟላ ባለመቻሉ፣ ታራሚዎች ክብራቸውን ከሚያዋርድና ፍጹም ኢ-ሰብዓዊ ከሆነ አያያዝ ተጠብቀው ሲፈጸም ከነበረው አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

ለማስቀረት በሚያስችል ቁመና ላይ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ሌላ ዐዋጁ ታራሚዎች በማረሚያ ተቋማት ውስጥ የሚያገኙት አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀና መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን አሟልቶ ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚመጥን መልኩ እንዲቀርብ ለማስቻል፣ የጤና፣ ትምህርት እና ሥራ የመሳሰሉት አገልግሎቶች ውስንነትን በማስቀረት ሁሉም የሕግ ታራሚዎች በፍትሐዊነት እንዲጠቀሙ የሚያስችል አሠራር ለመዘርጋትና በቆይታቸው የዕውቀትና የሙያ ባለቤት እዲሆኑ ለማስቻል በበቂ ሁኔታ አለመዘጋጀቱ ጥያቄ ይነሳበት ነበር፡፡ ከዚህ አንጻር ከላይ የተነሱትን ትችቶች እንዲሁም ታራሚዎችን ወደ ማኅበረሰቡ የመቀላቀል ኂደቱን ለማቀላጠፍና ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ ለማስቻል በሚሉ ዋና ዋና ምክንያቶች መነሻነት በሥራ ላይ ያለው ዐዋጅ ሊሻሻል ይገባዋል በሚል ረቂቁ መዘጋጀቱን ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በቅርቡ ከቀረበው ማብራሪያ እና ረቂቅ የሕግ ሰነዱ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው በዐዋጁ ማሻሻያ ይደረግበታል ተብሎ የሚታሰበው ጉዳይ የማረሚያ ተቋማቱን የሚያስተዳድረውን አካል የተመለከተው ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በሥራ ላይ ባለው ዐዋጅ ይህ ኃላፊነት "በፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር" ሥር ሲሆን ይኸው ተቋም የሕግ ታራሚዎችን ከማስተዳደር ባለፈ ወደ ማኅበረሰቡ የሚቀላቀሉበትን ልዩ ልዩ የሥነ-ልቦናና የሕይወት ክሒሎት የመገንባት ኃላፊነት ያለበት ከመሆኑ አንጻር ረቂቁ ሕግ ይህንኑ ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ በሚያስችል አደረጃጀት እንዲዋቀር የሚያስችል ድንጋጌ ይዟል፡፡ ከእነዚህም መካከል ተቋሙ ወደ ኮሚሽንነት እንዲያድግ የሚያደርግ፣ ከክልል ማረሚያ ቤቶች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በተመለከተ በትብብር የሚሠራባቸውን መንገዶች የሚያመላክት፣ በተቋማቱ ውስጥ እንደ አዲስ በሚዘረጉ የአንደኛ ደረጃ፣ የጎልማሳ፣ የመሰናዶ እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶችና ማዕከላትን አደረጃጀት የሚወስንበት፣ ከግብርና እና እንስሳት እርባታ በተጨማሪ ወደ አግሮ ኢንደስትሪ ለማሳደግ የሚጠበቅበትን ድርሻ የሚያሳይ፣ እና ብቁና በርካታ የማረሚያ ፖሊስ ሠራዊት ለማደራጀት የሚያስችለውን አቅምና ሌሎች ጉዳዮችን የተመለከቱ በርካታ ማሻሻያዎች ተደርገውበት ተዘጋጅቷል፡፡

የትርጉም ማሻሻያን በተመለከተ በዋናነት "ማረሚያ ቤት" የሚለውን በራሱ ረቂቁ ሕግ አዲስ ትርጉም ሰጥቶት ብቅ ብሏል፡፡ በሥራ ላይ ባለው ዐዋጅ አንቀጽ 2/4 ሥር ማረሚያ ቤት ማለት "በፍርድ ውሳኔ ታራሚዎች የእሥር ቅጣታቸውን የሚፈጽሙበትና በፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚላኩ ውሳኔ እስከሚያገኙ እንዲቆዩ የሚደረግበት ነው" የሚል ሲሆን፤ በረቂቁ "ማረሚያ ቤት ማለት፡- ለሕዝብ በግልጽ የሚታወቅና ታራሚዎች የተወሰነባቸውን ፍርድ የሚፈጽሙበት፣ የሚታረሙበትና የሚታነጹበት ሲሆን ማረፊያ ቤትን ይጨምራል" ይላል፡፡ ይህም በተለይ በቅርብ ጊዜ እንደታዘብነው ከሕዝብም ከመንግሥትም የተሸሸጉ ድብቅ እስር ቤቶችን በተመለከተ በእንደነዚህ ዓይነት ሥውር የማሠቃያ ቤቶች ውስጥ የተሰማሩ ግለሰቦችን ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ይረዳል ተብሎ በታሰበ መንገድ እንደተዘጋጀ ማብራሪያው ይጠቅሳል፡፡ ሆኖም እዚህ ጋር አሁንም ጥያቄ ሊያስነሣ የሚገባው ነጥብ እንደዚህ ዓይነት ሥውር የማሠቃያ ቤቶችን በተመለከተ መንግሥት ከሕግ ማሻሻያ በተጨማሪ ለአንድ ሰሞን የብዙኃን መገናኛ ወሬ በዘለለ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያደርግበት አሠራር ሊኖር እንደሚገባ ማሳሰብ ተገቢ ነው፡፡

ከዚሁ ከትርጉም ጋር አያይዘን ብናየው መልካም የሚሆነው ሌላው ነጥብ ረቂቁ ሕግ ለታራሚ፣ መደበኛ የቀጠሮ እሥረኛ እና ለቀጠሮ እሥረኞች ለእያንዳንዳቸው የተለየ ትርጉም እንዲሰጥ ሆኖ መዘጋጀቱን የተመለከተው ነው፡፡ ይኸም በተለይም ጉዳያቸውን በፍ/ቤት እየተከታተሉ ባሉ እና ፍርድ ተሰጥቷቸው እየታረሙ ባሉ ሰዎች መካከል የሚኖረውን ጉልሕ ልዩነት በሕግ ፊት እንደ ንጹሕ የመታየትን መርሕ (The Principle of Presumption of Innocent) በጠበቀ መልኩ እንዲሆን መደረጉ መልካም የሚባል ነው፡፡

ረቂቁ አዲስ ካስተዋወቃቸው አሠራሮች አንዱ በማኅበረሰቡ ዘንድ የታወቁና ተቀባይነት ያላቸው በጎ ፈቃደኛ ግለሰቦችን፣ የሃይማኖትና ባሕላዊ ሥርዓት መሪዎችን፣ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾችን፣ እና ታዋቂ ግለሰቦችን ያካተተ ኮሚቴ የታራሚዎችን አያያዝ እንዲከታተሉና እንዲቆጣጠሩ ዜጎችም ለተቋሙ ያላቸውን ዕይታ ለመቀየር በሚያስችል መልኩ እንደሚዋቀር ያስቀምጣል፡፡

የታራሚዎችን አያያዝ በተመለከተ ረቂቁ በመርሕ ደረጃ በታራሚዎች መካከል ልዩነት አለማድረግ፣ ጭካኔ ከተሞላበት አያያዝ የመጠበቅ፣ ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚመጥን ሁኔታ መያዝን እና ወደ ማኅበረሰቡ የመቀላቀል ሥራን የተቋሙ መርሖዎች እንዲሆኑ ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡ የታራሚዎች መኖሪያ ክፍሎችም በቂ ስፋት እንዲኖራቸው፣ ንጹሕ አየር የሚያስገቡና በቀን ለማንበብ የሚያስችል የተፈጥሮ ብርሃን በምሽት ደግሞ በቂ ብርሃን እንዲኖራቸው፣ ለእያንዳንዱ ታራሚም አልጋ፣ ፍራሽና ብርድ ልብስ በመንግሥት እንዲሟላ እንደሚደረጉ ደንግጓል፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪም ረቂቁ ሌሎች ዝርዝር ማሻሻያዎችን ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ ቢሆንም ለዛሬ በአጭሩ ያደረኩትን ዳሰሳ እዚህ ላይ አበቃለሁ፡፡ ቸር ቆይታ!

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።


# ቀለም

//

## ኢሰመጉ በመሥራቾች ዕይታ

(ከአቶ አበበ ወርቁ 27/3/2012 ካደረጉት ንግግር የተወሰደ ለመልዕክተ ኢሰመጉ በሚሆን መልኩ የተዘጋጀ)

ዳን ይርጋ



የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) የተቋቋመው የደርግ 17 ዓመታት አገዛዝ አልፎ የኢህአዴግ መንግሥት ከተተካ በኋላ ማለትም በ1984 ዓ.ም ላይ ነው፡፡

ኢሰመጉ በሚቋቋምበት ወቅት አንጻራዊ ነጻነት የተሰጠ የሚመስል ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ቢሆንም በአንፃሩ ደግሞ ከፍተኛ ሥርዓት አልበኝነት፣ የሙብት መጣሶች፣ በሕግና በሥርዓት ማስተዳደር ሳይሆን መንግሥት በጉልበት፣ በመሐይማንና በጠብ መንጃ መግዛት የጀመረበት፣ ሰዎች ያለ ሕግ በየመንገዱ እየተገደሉ፣ እየተደበደቡ፣ እየተሰቃዩ የነበረበት አስቸጋሪ ጊዜ ነበር፡፡

ከላይ በተጠቀሰው አስቸጋሪ ወቅት ነው እንግዲህ ኢሰመጉ በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሐሳብ አመንጭነት እርሳቸውን ጨምሮ 32 አባላት ከየሙያው

ተሰባስበው ኢሰመጉ የተቋቋመው፡፡ ዓላማው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ለማጋለጥ በመሆኑ ይህም በመንግሥት በመታወቁ እንዳይቋቋም የተለያዩ ጫናዎችና እንቅፋቶች ሲደረጉበት ለረጅም ጊዜ ቆይቷል፡፡ ለምስረታው ለመሰባሰብ የሚከራየው ቤት እንኳን ሊያገኝ ባለመቻሉ ከባድ የችግር ጊዜ አሳልፎ ነበር፡፡

ኢሰመጉ አሁን በዋና ጽ/ቤትነት እየተጠቀመበት ያለውን ቦታ ልዕለ የተባለ ድርጅት ተከራይቶት የነበረ ሲሆን የዚሁ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የነበሩትና ኢሰመጉንም ከመሠረቱት አንዱ የሆኑት አቶ ዐሥራት ገብሬ የተባሉ ግለሰብ ኢሰመጉን በጽ/ቤታቸው ውስጥ አዳብለውት ነበር ኢሰመጉ ሥራውን የጀመረው፤ በኋላም ከብዙ ጊዜ በኋላ ጽ/ቤቱን ወደ ራሱ ስም እንዲዞርለት ሆኗል፡፡

በምዝገባ ሂደቱም ቢሆን ኢሰመጉ ከባድ ሁኔታዎችን አሳልፏል፡፡ በወቅቱ ምዝገባውን የሚያካሄደው የሠራተኛና ማኅበራዊ ሚኒስቴር ኢሰመጉን አንዴ ‹‹የንግድ ድርጅት ነህ››፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ‹‹የፖለቲካ ፓርቲ ስለሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚመዘግብ ተቋም ሲቋቋም እዛ ሄዳችሁ ተመዝገቡ›› በማለት ለረጅም ጊዜ የኢሰመጉን አባላት አጉላልተዋል፡፡

ኢሰመጉ ተመዝግቦ ሥራ ሲጀምር ወጣት ፈቃደኛ መርማሪዎች ያለምንም ደመወዝ ተሰማርተው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲያጣሩ በራሳቸው ላይ ይደርስባቸው የነበረው ማሳደድና እንግልት በጣም ፈታኝ ነበር፡፡

ይሁንና የኢሰመጉ መርማሪዎች በመንግሥት የደኅንነት ኃይሎች እየተፈጸመባቸው ያለውን ማስፈራሪያ፣ ማሳደድና እንግልት ሁሉ ተቋቁመው የሚፈጸሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በሆስፒታል ውስጥ በመግባት የተገደሉ ሰዎችን ፎቶ ግራፎችን በማንሣት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሪፖርት እንዲወጣ የበኩላቸውን አኩሪ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ እነዚህ የኢሰመጉ መርማሪዎች በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ተሠማርተው ይገኛሉ፡፡ የተወሰኑትም በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋችነታቸው የሚታወቁ ሆነዋል ከነዚህም ውስጥ አቶ ያሬድ ኃይለማርያም የሰብዓዊ መብቶች ስብስብ በኢትዮጵያ የሚባል ተቋም ዋና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም አቶ ወንድምአገኝ ጋሹ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ኢሰመጉ ከተመሠረተ በኋላ የተቋቋመው ቦርድ አባላት በየሳምንቱ አንዳንዴም በየዕለቱ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሰብዓዊ መብቶች ምርመራና የሪፖርት ዝግጅት ሥራዎችን ጥራት በመከታተል የበኩላቸውን እገዛ አድርገዋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ኢሰመጉ በስፋትና በብዛት እያጋለጠ አቅሙንም እያጠናከረ ሲመጣ የመንግሥት ዛቻ እና ክትትል በዚያው መልኩ እየጨመረ መጥቶ ነበር፤ በተለይም ፕሮፌሰር መስፍን ላይ ይደረግ የነበረው ክትትል ከፍተኛ ነበር፡፡ አንድ ቀን ፕሮፌሰር መስፍን መኪናቸውን እያሽከረከሩ በሚሄዱበት ወቅት የመንግሥት የደኅንነት አባላት ሲከታተሉዋቸው ከመኪናቸው ወርደው ‹‹ምንድን ነው የምትፈልጉት? ለምንድን ነው የምትከታተሉኝ? የምትፈልጉት ነገር ካለ ይኸው አድርጉ›› ብለው ምርር ብለው የተናገሩበት ገጠመኝ ነበር፡፡

ኢሰመጉ ከፍተኛ የሆነ በደሎች በመንግሥት ሲፈጸምበት የቆየ ተቋም ነው፤ ለምሳሌ በባንክ ሒሳብ የነበረ ሰባት መቶ ሺ ብር የሚገመት ገንዘብ ታግዶበት ነበር፡፡ እንዲሁም፣ የቢሮ በር እየተሰበረ ኮምፒውተሮችና ሌሎች የቢሮ መገልገያ ማሽኖች ዝርፊያ ተፈፅሞበታል፣ አአመራሩና አባላቱ በተለያዩ ጊዜያት ታሥረዋል፡፡

እንደነ አሰፋ ማሩ ያሉ የኢሰመጉ የቦርድ አባል በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች ተገድለዋል፣ አቶ አበበ ወርቁን ጨምሮ በርካታ የኢሰመጉ አመራርና አባላት በመንግሥት ጫና እና የተለያዩ ድርጊቶች ሐገር ለቅቀው እንዲወጡ ተደርገዋል፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን ለበርካታ ዓመታት ኢሰመጉን በጥንካሬና በትጋት ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ‹‹ኢሰመጉ መስፍን ብቻ አይደለም›› በማለት ከአመራርነታቸው ሲለቁ በምትካቸው ፕሮፌሰር አንዳርጋቸው መሳይ ሲተኩ አቶ አበበ ወርቁም በምክትል የቦርድ ሊቀመንበርነት እንዲሁም በዋና ጸሐፊነት ደግሞ ዶ/ር መኮንን ቢሻው በርካታ አኩሪ ሥራዎችን አከናውነዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ አበበ ወርቁ ከዘጠኝ ዓመት የስደት ቆይታ በኋላ የተፈረደባቸው ፍርድ ተሸሮላቸው ወደ ሐገር በመመለሳቸው ደስታ እንደፈጠረባቸው በመግለጽ ኢሰመጉ በበርካታ አባላቱና ደጋፊዎቹ ብዙ ሥራዎችን አከናውኗል አሁን ግን የአባላትና የደጋፊዎቹ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል ይህም ሊታሰብበት ይገባል በማለት ንግግራቸውን ቋጭተዋል፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።